# እናስብሻለን!

(ለብርቱካን ሚደቅሳ)




ይሰማናል ድምጽሽ!
                    ሙዚቃዊ ቃና
እንደ ዘለሰኛ ወይ እንደ መዲና...
እሚተም ከሩቁ ልክ እንደ በገና።

---

ባንሰማ እንመርጣለን!
ግን ጆሮ ይሰማል..፤
ጥዑሙን ሙዚቃ እሚረብሽ ሆታ፣
አንዳች መዐት ጩኸት የመልቲ ኳኳታ።
        ይጠራል ጫጫታው፤
        የጊዜ ጉዳይ ነው።

---

ያንቺ ግን ሙዚቃ. . .
ውስጥሽ የፈለቀ አገራዊ ዜማ፣
ከጽንፍ-አጽናፍ ዘልቆ ጎልቶ እሚሰማ፤
ጥንተ-ያሬዳዊ ዕዝልና አራራይ. . .፣
የኢትዮጵያ ስጦታ ከሰማየ-ሰማይ!
እንደ አባይ እንደ ኦሞ፣ እንዳዋሽ ተከዜ. . .፣
ባገር ምድሩ አፈር ይፈሳል ሁል ጊዜ።

እንደ ክራር ድርድር እየኮረኮረ፣
እንደ ዋሽንት ትንፋሽ ነፍስ እያማለለ፣
እንደ መሰንቆ ድምጽ ልብ እየመሰጠ..፣
ለሁሉ ይዳረሳል፤
መንፈስን ያድሳል።

ይታየናል ፊትሽ!
        ገጸ-ትህትና
ብሩህ ደማቅ ፋና. . .
በግልጽ እሚነበብ ልክ እንደ ብራና።

---

ባናይ እንወዳለን!
ግና ይታየናል፤
የጨፈገገ ፊት ክፋት የወረሰው፤
የፈካውን ፊትሽን በግድ ሊያጨልመው፤
ክፉ እማይወጣውን አፍሽን ሊያረክሰው፤
በሕዝባዊነትሽ ከምር ተቆጭቶ፤
በክፋት ሲኳትን ሊያጠቃሽ አድብቶ፤
ንጹህ አእምሮሽን ሊበክል ሲቃጣ፣
ይታየናል ደግሞ ሲያስነሳን በቁጣ።
እምነትሽ ላይ ላይደርስ እንዲሁ ይለፋል፤
ህሊና ቢኖረው በዓለም ፊት አፍሯል!

---

ይሰማናል ድምጽሽ! ይታየናል ምስልሽ. . .
በዕለት. . . በዕለቱ . . .
ተመርጠሻል አንቺ ለአገር ስምረቱ!
የመዝሙርሽ አዝማች «ቃሌ» ተዘምሯል፤
በሕብረ-ዜማ ጣዕም ባለም አስተጋብቷል።
አገር ይሰማሻል! አገርም ያይሻል!
ዓለም ያስብሻል!
በርቺ! እህት አለም
ያሰብሽው ዓላማ ይስመር ለዘልዓለም!!

ጌታቸው አበራ - ግንቦት 2002 ዓ/ም (ሜይ 2010)